በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# እግዚአብሔር አለ!

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ
**E-mail:** kesisolomon@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**የካቲት ፲ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**

# እግዚአብሔር አለ!

## *መግቢያ*

- አማንያን ሁሉ እግዚአብሔር እንዳለ ያምናሉ፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የምንመለከተው እግዚአብሔር በሕይወታችን ስለ መኖሩና ስለሚሠራውም ነው፡፡

- እግዚአብሔር አለ ማለት ያየናል፣ ይሰማናል፣ የሚሆነውንም ያውቃል … ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ይቆጣጠራል ነገሮችንም ባሉበት ሳይተዋቸው መፍትሔ ይሰጣቸዋል፡፡

- እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ፣ በየትኛውም ሁኔታና አጋጣሚ ከእያንዳንዳችን ጋር አለ፡፡ በገጠመን ሁሉም ሁለም ሆነ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን እጅ በግልጽ ስናይ ኖረናል፡፡

- እግዚአብሔር በሕይወታችን ጉዳይ ሁሉ ጣልቃ እንደገባልን እንደሚገባልንም እናምናለን፡፡

- አብዝተን ከሰዎች ጋር አንመክርም ነገር ግን ከርሱ ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ጋር ግን በጸሎት እንነጋገራለን፡፡

- “ትመልስልኛለህና በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጠራለሁ።” *መዝ 85:7 ::*

- “አቤቱ፥ አንተን ጠርቻለሁና አልፈር ከፉዎች ይፈሩ በሲኦልም ዝም ይበሉ።” *መዝ 31:17::*

- “አቤቱ፥ አንተን ከጥልቅ ጠራሁህ።” *መዝ 129:1::*

# እግዚአብሔር አለ!

## *እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ሆኖ አለ ይኖራልም*

- ሁሉን ቻይ ነው ማለት ሁሉ ከእጁ በታች ነው፣ ሁሉ በአገዛዙ ሥር ነው ማለት ነው፡፡ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ናቸው፡፡
- ዲያቢሎስና የክፋት ኃይል ሁሉ እንኳ ሳይቀር ገደብ በሚያደርግባቸው በእርሱ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ናቸው፡፡
- እግዚአብሔር ጣልቃ የማይገባ ቢሆን ኖሮ ብርቱው ደካማውን እየበላ ሰዎች በምድር ላይ ለመኖር ባልቻሉ ነበር፡፡
- ዓለሙን የፈጠረው እርሱ ነው፡፡ ፈጥሮም አልተወውም ዓለሙን በውስጡ ያሉትን ሁሉ ይቆጣጠራል እንጂ፡፡
- አሁንም ለሁሉም የምንለው ብቻችሁን አይደላችሁም ነው፡፡ ሕይወትን እየኖራችሁ ነው እግዚአብሔርም ከእናንተ ጋር ነው፡፡ እርሱም ለአንዲት አፍታ ለዓይን ጥቅሻም ቢሆን አይተወንም፡፡
- "እነርሱም እጁን አላሰቡም፥ ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳነበትን ቀን ።" *መዝ 77፡42፡፡*
- "እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥላቸውም የምድር ዳርቻዎችም በእጁ ውስጥ ናቸው፥ የተራሮች ከፍታዎች የእርሱ ናቸው።" *መዝ 94፡4፡፡*

## *እረኛችን ነውና እግዚአብሔር አለ*

- ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።" *መዝ 22፡1-3፡፡* **ብሏል**፡፡
- **እግዚአብሔር በተጨማሪ** "እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ አስመስጋቸውማለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡- የጠፋውንም እፈልጋለሁ የባዘነውንም እመልሳለሁ የተሰበረውንም እጠግናለሁ የደከመውንም አጸናለሁ የወፈረውንና የበረታውንም አጠፋለሁ በፍርድም እጠብቃቸዋለሁ።" *ሕዝ 34፡15-16፡፡* **ብሏል**፡፡
- **እግዚአብሔር ለእኛ በሚያደርግልን ጥበቃ እንታመናለን፡፡ በነገርም ሁሉ እንታመንበታለን፡፡ መንጋውንም** "እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።" *ዮሐ 10፡28-29፡፡* **ባለ እንታመናለን**፡፡

# ጠባቂያችንና ረዳታችን እግዚአብሔር አለ!

በመዝሙረ ዳዊት "ዓይኖቼ ወደ ተራሮች አነሣሁ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም የሚጠብቅህም አይተኛም። እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም። እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፥ እግዚአብሔርም በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል። ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም ጨረቃም በሌሊት። እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፥ ነፍስህንም ይጠብቃታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህና መግባትህን ይጠብቃል።" **በማለት ጠባቂ መላእክቶቻችን ሲጸልዩልን የሚናገሩትን በመውሰድ እኛም ስንጸልይ ራሳችንን ለማጽናናትና ለማረጋጋት ስንል ይህንኑ ደግመን በየጸሎታችን እናነሳዋለን::** *መዝ 120:1-8::*

- **እግዚአብሔር ለአባታችን ለያዕቆብ** "እነሆም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ በምትሄድባትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፥ ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁ የነገርሁህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህም" *ዘፍጥ 28:15::* **ብሎታል::**

- **ዮናስን በዓሳ አንበሪው ሆድ ውስጥ ሳለው የጠበቀው፣ ሦስቱን ወጣቶች ጠጉራቸውና እንኳ ሳይቃጠል ከነበልባሉ የእቶን እሳት የጠበቃቸው እርሱ እግዚአብሐየየር ነው:: ዳንኤልንም ከአንበሶች መንጋጋ ጠብቆታል::** "በፊቱ ቅንነት ተገኝቶብኛልና፥ በአንተም ፊት ደግሞ፥ ንጉሥ ሆይ፥ አልበደልሁምና አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ፥ እነርሱም አልጐዱኝም አለው።" *ዳን 6:22::*

- **ዮሴፍን ወንድሞቹ በጉድጓድ ሲጥሉት፣ በጵጥፋራ ቤት በባርነት ተሽጦ ሲያገለግል የጠበቀው፤ በእስር ቤት ሲጣል ክብሩን አብዝቶ መልሶ የሰጠው በመጨረሻምመ ለወንድሞቹ** "እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው።" **ለማለት ያበቃው አምላካችን እግዚአብሔር ነው::**

- **እግዚአብሔር ከዲያቢሎስ፣ ከኃጢአት፣ ከፈተኛ ሁሉ ጠብቆናል ብለን እናምመናለን:: ቅዱስ አትናቴዎስን አራት ጊዜ፣ ቅዱስ ዮሐንስን በፍጥሞ ደሴት ሲጋዙ የጠበቃቸው እርሱ ነው::ሕጻናትንም ይጠብቃቸዋል::** "እግዚአብሔር ሕፃናትን ይጠብቃል ተቸገርሁ እርሱም አዳነኝ።" *መዝ 115:6::*

- **እግዚአብሔር እንዳለ እንደሚጠብቀንም ከዘነጋን እንታወካለን:: እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገው ረጅም ጥበቃ ዘመናትን ያስቆጠረ የማይረሳ ታሪክ ነው:: እያንዳንዳችን በፊቱ ሆነን ምን ያህል ጊዜ እንደጠበቀን በማስታወስ** "ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ አጥንቶቼም ሁሉ፥ የተቀደሰ ስሙን። ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ" *መዝ 102:1-2::* **ማለት ይኖርብናል::**

# ሁሉን የሚጠብቅ እግዚአብሔር አለ!

- አምላካችን "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።" **ብሎናል::** ***ማቴ 11:28::***

- **በመዝሙረ ዳዊትም** "ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፥ እርሱም ይደግፍሃል ለጻድቁም ለዘላለም ሁከትን አይሰጠውም።" ***መዝ 54:22::*** "በመከራ ቀን እግዚአብሔር ይስማህ የያዕቆብ አምላክ ስም ያቁምህ።" ***መዝ 20:1::***

- **አዎ የምንታመንበት እግዚአብሔር "የተጨነቁትን የሚያረጋጋ... አባት እናት የሞቱበትን የሚቀበል... " ነውና** "እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ በርታ፥ ልብህም ይጽና እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።" ***መዝ 27:14::***

- **አምላካችን ለእንስሳቱና ለአዕዋፋቱ፣ በድንጋገይ ሥር ለምትኀዘው ለትልዋ እንኳ ያስባል::** "ለሚጠሩት ለቍራዎች ጫጩቶች ለእንስሶችም ምግባቸውን ይሰጣል።" **መዝ 146:9:: የማይፈትሉትንና የማያጭዱትን አእዋፋትም የሰማዩ አባታችን ይመግባቸዋል:: ማቴ 6:26::** "ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም።" **ማቴ 10:29:: በኖኅ መርከብ ውስጥ የነበሩትን... ቢራቢሮዎቹንም ውብ ቀለም ሰጥቷቸዋል::** "ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም።" **ማቴ 6:29:: ለሚዘምሩት አዕዋፋት ሳይጠይቁት ምልካም ድምጽ ሰጥቷቸዋል፣ ... ታዲያ ለሰውስ ምን ያህል ይጠነቀቅለት ይሆን::**

- **እኛ ለራሳችን ከምናደርገው በላይ እግዚአብሔር ይጠነቀቅልናል::** "አልጥልህም፥ አልተውህም።" ***መዝ 115:6::*** "በውኑ ሴት ከማኅፀንዋ ለተወለደው ልጅ እስከማትራራ ድረስ ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን? አዎን፥ እርስዋ ትረሳ ይሆናል፥ እኔ ግን አልረሳሽም።" ***ኢሳ 49:15::*** **ባለን ታምነን እንኖራለን፤ በመላእክቱ አጥሮ ይጠብቀናልና::** ***መዝ 33:6-8::***

- ***መዝሙረ ዳዊት*** "በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል።" ***መዝ 90:11-12::*** **እንዳለ::**

# እግዚአብሔር አለ! ስንል ደግነቱንና ርኅራኄውን በማሰብ ነው

- እግዚአብሔር ለእንስሳቱና ለአእዋፋቱ የሚራራላቸው ከሆነ ለሰውስ ያለው ርኅራኄው እንዴት ያለ ይሆን?

- ከደግነቱ የተነሳ ነው ለሰው አእምሮን፣ ነፍስንና ነጻ ፈቃድን የሰጠው፡፡ ኅሊናንም ሰጥቶታል፡፡ ዘላለማዊ ሕይወትንም አዘጋጅቶለታል፡፡ በረከትን፣ ሥልጣንን... ሳይጠይቅ ስጦታን ጠይቆም ከጠየቀው በላይ አብዝቶ ሰጥቶታል፡፡ ቢያለቅስ ዕንባን ሁሉ ከሰው ዓዐዐን ይጠርጋል፡፡

- **እግዚአብሔር ደግ አምላክ ከሆነነ መከራ ይመጣብን ዘንድ ለምመን ይፈቅዳል? የሚፈቅደው ከጥቅማቸው የተነሳ ነው፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ** "ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፡፡" *ያዕ 1፡2፡፡* **ወደ እኛ ከሚመጣው ከእያንዳንዱ ፈተና ጀርባ ያለውን ምክንያትና እንዴትም እንደምትወጡት እወቁ ወይም አስተውሉ፡፡ በፈተና ከሚገኙ ጥቅሞች መካከል ጥቂቶቹን ለመግለጽ፡-...**

1. **በአንድ ልብ በርኅራኄ እንድንተሳሰር እንድንቀራረብ ያደርጋል፡፡**
2. **ፈተና ሲመጣ ውስጣዊ ማንነታችንን በመመርመር ራሳችንን እናስተካክላለን፣ ከሌሎች ጋር ያለንን አለመግባባትም እናርማለን፣ ርቀን ከነበርም ከእግዚአብሔርም ጋር እንታረቃለን፡፡ በፈተና ጊዜ ሰዎች በጾማቸው, ቅዱስ ቁርባን በመቀበል... ከእግዚአብሔር ጋር እንደ እንግዶች ሳይሆን እንደ ልጆቹ ቀርበው ሲታረቁ ተመልክተናል፡፡** "ወደ እኔ ተመለሱ፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ" እንዳለ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
3. **ነገሮችን ግልጽ ያደርግልናል አጥርተን ማየትም ያስችለናል፡፡ በፈተና ወዳጅና ጠላታችንን እንለያለን፡፡**
4. **በፈተና የእግዚአብሔር እጅ ከእኛ ጋርና ከሌሎችም ጋር ሲሰራ እናይበታለን፡፡**
5. **በፈተና መንፈሳዊ ልምዶችን ከእግዚአብሔር የምናገኝ ስንሆን ለመልካምመ ዕድሎችም ጥሩ አጋጣሚ ነው፡፡ ፈተና ትምህርት ቤት ነው፡፡ የሚፈተኑ በዕውቀት፣ በጥበብናነ በልምድ ያድጋሉ ችግሮቻቸውም በርሱ እንዴት እንደሚፈቱ ያያሉ፡፡** "ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላልና አለ።" *ማር 10፡27፡፡*
6. **ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሆነ እናውቅበታለን፡፡ ሮሜ 8፡28፡፡** "ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።" **1ኛ ቆሮ 10፡13፡፡**
7. **ዘወትር ፈተናን በረጋ ልቦና እንድናይ ያደርገናል፡፡ ፈተናነው ሲከብደን በእግዚአብሔር እጅ እናደርገዋለን፡፡ እግዚአብሔርን በፈተናችንና በእኛ መሐል አድርገን ፈተናውን ማየት እናቆማለን፡፡ የተቀረውንም ሁሉ እርሱ ይፈታልን ዘንድ በእጁ እንተወዋለን፡፡ እግዚአብሔር አለ!!! ይፈታልናል!!! ዘወትር ተግተን እንጸልይ!!!**

ይቆየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።